፲፭ እናንተ፡የፊልጵስዩስ፡ሰዎ
ች፡በመጀመርያ፡ትምርት፡ወ
ደ፡መቄዶንያ፡በመጣሁ፡ጊዜ፡
ከምእመናን፡እንዱስ፡ስንኳ
እሱ፡በመስጠት፡እኔ፡በመቀበ
ል፡ከኔ፡ጋራ፡እስኪድ፡እንዳልሆ
ኑ፡ታውቃላችሁ፡እናንተ፡ብቻ
ናችሁ፡እንጂ፨፩፡ጢሞ፡፩፡፫፡፪
፲፮ ቆሮ፡፲፩፡፱፨በተሰሎንቄም፡ደ
ጋግም፡እንድ፡ጊዜ፡ሁለት፡ጊዜ፡ለ
ችግሬ፡ነገር፡ላካችሁልኝ፡
፲፯ የሐዋ፡፲፯፡፩፨ይህንም፡የምና
ገር፡ስጦታችሁን፡ስሻ፡አይደለ
ም፡በናንተ፡ላይ፡የጽድቅ፡ፍሬ
ይበዛ፡ዘንድ፡ወድጄ፡ነው፡እንጂ
፩፡ቆሮ፡፱፡፲፩፡ቲቶ፡፫፡፲፬፨
፲፰ እነሆ፡የላካችሁልኝን፡ሁሉ፡
ተቀበልሁ፡ለለት፡ምግቤ፡በቃ
ኝ፡በተረፈውም፡ጉደዬን፡ፈጸ
ምሁ፨በእግዚአብሔር፡ዘን
ድ፡የተወደደ፡የተመረጠ፡በጎ
መዓዛ፡ያለው፡መሥዋዕት፡እ
ድርጎ፡ከናንተ፡ወገን፡የሚሆነ
እፍሮዲጡ፡ስላመጣልኝ፡ም
፪፡፳፭፡ኤፌ፡፭፡፪፡ዕብ፲፫፡፲፮፨
፲፱ የምትሹትንም፡ሁሉ፡እምላ
ኬ፡ይፈጽምላችሁ፡እንደ፡ኢየ
ሱስ፡ ክርስቶስ፡ ክብር፡ብዘ
፳ ተኃ፪፡ቆሮ፡፱፡፰፨እንደ፡እግዚ
አብሔርም፡ቸርነት፡የዘለዓለ
ም፡ምስጋና፡ለሱ፡የሚሆን፡

፳፩ ቅዱሳንን፡ሁሉ፡በኢየሱስ፡ክር
ስቶስ፡ሰላምታ፡እንዴት፡ናችሁ
ብሉ፡ከኔ፡ዘንድ፡ያሉ፡ወንድሞ
ቻችን፡እንዴት፡ናችሁ፡ይሏች
፳፪ ኋል፨፩፡ቆሮ፡፲፮፡፳፡ቅዱሳን፡ሁ
ሉ፡ይልቁንም፡በቄሣር፡ቤተ፡
መንግሥት፡ያሉ፡ሰዎች፡ሁሉ
እንዴት፡ናችሁ፡ይሏችኋል፨
፪፡ቆሮ፡፲፫፡፲፪፨
ወንድሞቻችን፡የጌታችን፡የ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጸጋው፡ከ
ናንተ፡ጋራ፡ይሁን፨፩፡ቆሮ፡፳፡
፲፫፡ቆላ፡፬፡፲፰፨
በሮም፡የተጻፈች፡በጢሞቴ
ዎስና፡በአፍሮዲጡ፡እጅ፡ወደ
ፊልጵስዩስ፡ሰዎች፡የተላከ
ች፡የጳውሎስ፡መልእክት፡ተ
ፈጸመች፨ ፨ ፨
አስጀምሮ፡ላስጨረሰኝ፡ለእ
ግዚአብሔር፡ክብር፡ምስጋ
ና፡ይግባው፨ ፨ ፨

